

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

# ከማርች 1-31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

# እንዲሁም ከኤፕሪል 1-30/2025 የሚኖረው የአየር ጠበይ ትንበያ

# እና ምክረ ሃሳብ

ኤፕሪል 2025

አዲስ አበባ

## 1.1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ

ባሳለፍነው የማርች ወር በተለይም በሁለተኛው አስር ቀናት እና በሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት በደቡብ፣ በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ በሰሜን ምዕራብ፣ እና በደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን እና ክምችት ነበራቸው፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ፣ በመካከለኛው፣ በሰሜን ምዕራብ እና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል በአርባምንጭ 26.5፣ 11.4፣ 10.1፣ በሀዋሳ 29.5፣ 20.2፣ በኮምቦልቻ 27.7፣ 26.9፣ በደብረ ብርሃን 16.8፣ በደብረ ማርቆስ 19.2፣ 15.8፣ 14.2፣ 20.7፣ በጎዴ 39.6፣ በጅማ 10.6፣ 14.5፣ 12.2፣ 36.7፣ 15፣ 22.9፣ በመተሃራ 39፣15.8፣ 10.7፣ በነገሌ 17.2፣ 14.1፣ 42.5፣ በነቀምት 12፣ 10.7፣ በሮቤ 17፣ በአቦምሳ 12፣ በአዲስ አበባ ቦሌ 10.9፣ 19፣ በአዲስ አበባ ጥቁር አንበሳ 34.5፣ 12.5፣ 16.4፣ በአጽቢ 11.0፣ 11.2 በአደዋ 18.6፣ በአዲግራት 44.7፣ 26.7፣ በሀሮማያ 17.4፣14፣ በአለም ከተማ 10.4፣10.6፣ 54፣ በአማን 14.2፣ 12.7፣11.2፣ 20.2፣ 29.1፣ 13.3፣ በአምባ ማሪያም 18.4፣ 12.6፣ 11.2፣ 24.6፣ 18.4፣ በአምቦ 14.5፣ 11.3፣ 22.7፣ በአምደ ወርቅ 34፣ በአርጆ 16.4፣ 26.2፣ 16.6፣ 24.2፣ 36.4፣ 24.2፣ 28.6፣ 26.4፣ በአርሲ ሮቤ 12፣ 11.3፣ 17.8፣ በአደሌ 54፣ በአዋሽ አርባ 11፣ በበደሌ 26.2፣ በብላቴ 13.8፣ 18.5፣ በቦሬ 14.2፣ 11.1፣ 47.5፣ 17.1፣ 16.4፣ በቡሂ 31፣ 46፣15.5፣ በቡሬ 22.6፣ በባቲ 38፣ በቡርጂ 10.7፣ 57.2፣ 10.1፣ በጭራ 13.5፣ 17.5፣ 14.4፣ 53.5፣ 14.3፣ 11.2፣ በደምቢ ዶሎ 12.5፣ በዲላ 5.7፣11፣ 25.6፣ 16.4፣ 35.6፣ 14.2፣ በዶሎመና 10.5፣ 40.3፣ 10.5፣ በኢጃጂ 42.9፣ 18.2፣ በእነዋሪ 29.5፣ 12.3፣ በፍቼ 24.8፣ 11.6፣ በፉኙዶ 12.9፣ 14.3፣ በጋቲራ 14.8፣ 22.6፣ 28፣12.2፣ 25.4፣ 35.8፣ 14.6፣ 14.7፣ 16.2፣ በገለምሶ 57.5፣ 24.2፣ 15.7፣ በገዋኔ 59.9፣ በወሊሶ 24.7፣ በጊደ አያና 24.1፣ በጊኒር 44፣10፣ 40፣ 42፣ 26፣ በጉንዶ መስቀል 18.2፣ በቡሌ ሆራ 27.4፣ 13.7፣ 49.3፣ 11.2፣ 44.2፣ በሐረር 10.6፣ 16.5፣ 17.4፣ በሆሳዕና 14፣ 38.6፣ 38.3፣ 26፣ 21.7፣ 12.5፣ 18.2፣ 23.5፣ 21.8፣ 38.5፣ በእምድብር 17.1፣ 17.4፣ 51.4፣ 22.4፣ በጎሬ 14፣ 16፣ በጃራ 12.2፣ 18.8፣ 22.2፣ 41.1፣ 27.1፣ 26፣ 14.5፣ በጅግጅጋ 12፣ 38.2፣ 26፣ 16.2፣ በጅንካ 18፣ 19.7፣ 19.5፣ 11.2፣ 26፣ 15.9፣ 12.7፣ በካቺሴ 12.4፣ በኮንሶ 19.3፣14.4፣ 22.5፣ 15.5፣ 12.6፣ በቁሉምሳ 47.3፣ 12.4፣ በላሬ 12.2፣ በሊሙ ገነት 16.7፣ 13.8፣ 23፣ 12.7፣ በላሊበላ 10.6፣ በማይጨዉ 11.5፣ በማጂ 10.7፣




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

10.8፣ 15፣ 48.5፣16፣ 23.2፣ 24.2፣ 12.1፣ በማሻ 20፣12፣12.4፣ 20.4፣ 60.4፣ በመሀልሜዳ 16.8፣ በመኤሶ 11.5፣ 15.6፣ በመካነ ሰላም 15.3፣11.3፣ 38.2፣ በምዕራብ አባያ 15፣ 13፣ 11፣ በሞጣ 15፣ 36፣ በሞያሌ 12፣ 27.8፣ 28.4፣ 11.3፣ 48.4፣ በንፋስ መዉጪያ 11.1፣ 27.8፣ 19.2፣ በኑራ ኤራ 16.2፣ 16.4፣ በሳዉላ 50፣ 17.5፣ 16.6፣ 19፣ በሰኮሩ 15.5፣ 22.5፣ 13.2፣ 15.5፣ 20.7፣ በሻምቡ 11.7፣ በሲሪንቃ 11.2፣ 11.3፣ በቴፒ 15.1፣ 12.7፣ 22.6፣ በተርጫ 30.6፣ 16.2፣ 20.5፣ 17.3፣ 20.3፣ 12.2፣ 20.2፣19.5፣ 14.2፣ በጽጺቃ 12.4፣ በወገል ጤና 21.5፣ 16.6፣ በወራቤ 21.4፣ 21.8፣ 16.2፣ 49.9፣ በወረኢሉ 10.6፣ 14.7፣ 19፣ በወላይታ 40.7፣ 12.2፣ 13.9፣ በያቤሎ 57.1፣ 28.3፣ በየትኖራ 21.9፣ 12.3፣ በባቱ 10፣ 13.2፤ በጨለንቆ 20፤ በደንግጎ 15፣ በግራዋ 20፤ በዶሎ ኦዶ 15፣ በጉበይሬ 18.2፣ 25፣ በቀብሪ በያ 18.2፤ በሶካ 25፣ በመርሳ 14.8፣ በጉጉፉ 18.5፤ በወልዲያ 10.5፣ 23.8፤ በአቃስት 10.2፣ 16.3፣ 17፣19፤ በወገዲ 10.3፤ በከሚሴ 20.6፤ በማረያ 34.4፤ በሃረቡ 16፤ በጋሸና 22፤ በጃማዶጎሎ 11.5፣ 20.5፤ በአባዶ 45፤ በደበሌ 24.7፤ በጊናግረ 15.6፣ 24.6፣ 23.6፣ 15.9፣ ኩርፋጨሌ 19.9፣ 62.7፣ 14.4 ካራሚሌ 17.5፣ ሂርና 20፣ 29.8፣ 21.5፣ 22፣ 22.3፣ በግራዋ 13፣ 10.3፣ 15፣ 29 እንዲሁም በጊሸራቤል 11.2 ሚሜ የሚደርስ ከመካለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል።

በአጠቃላይ ባሳለፍነዉ የማርች ወር በ37 የሀገሪቱ አከባቢዋች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ የበልግ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 35-62.7 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ50 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ኩርፋ ጨሌ፣ ማሻ፣ ገዋኔ፣ ገለምሶ፣ ቡርጂ፣ ያቤሎ፣ አደሌ፣ አለም ከተማ፣ ጭራ፣ በእድብር፣ እንዲሁም ሳዉላ፣ ይገኙበታል (ምስል 1)፡፡




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





ምስል፡1 ከማርች 1-31 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ35 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባው ስፍራዎች

ባለፈዉ የማርች ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ አማሮ፣ ቡርጂ፣ አሊ፣ ኮንሶ ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የከንባታ፣ የሀዲያ፣ የሃላባ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦሮና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ባሌ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ የጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ የደቡብ እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ኖጎብ፣ ኤረር፣ ፋፈን እና የሲቲ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ ከአፋር ክልል የጋቢ፣ ሃሪ እና የማሂ ዞኖች ላይ ከ61-290 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ9-24 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2) ፡፡





ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ባለፈዉ የማርች ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ምዕራብ ኦሞ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል የደቡብ ኦሞ፣ ባስኬቶ፣ ጎፋ፣ ወላይታ፣ ጌዲዮ፣ አማሮ፣ ቡርጂ፣ አሊ፣ ኮንሶ ዞኖች ፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል የከንባታ፣ የሀዲያ፣ የሃላባ ዞኖች፣ ከኦሮሚያ ክልል ቦሮና፣ ምስራቅ ቦረና፣ ጉጂ፣ ምዕራብ ጉጂ፣ ምዕራብ አርሲ፣ ምስራቅ ባሌ፣ ምዕራብ ሐረርጌ፣ የጅማ፣ ቡኖ በደሌ፣ ኢሉባቦር፣ የደቡብ እና የምዕራብ ሸዋ ዞኖች፤ ከሱማሌ ክልል የዳዋ፣ ሊበን፣ አፍዴር፣ ሸበሌ፣ኖጎብ፣ ኤረር፣ ፋፈን እና ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜን ሸዋ ዞን፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ ዞኖች፣ ምስራቅ ጎጃም ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የመካከለኛዉኛ የምስራቅ፣ የደቡብ ምስራቅ እና የደቡብ ትግራይ ዞኖች መደበኛና ከመደበኛዉ በላይ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3) ፡፡





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት

በሌላ በኩል በፉኙዶ፣ በጋምቤላ፣ በላሬ፣ በመተማ፣ በጎዴ፣ በግዋኔ፣ በመተሃራ፣ በአዋሽ አርባ፣ በአይሻ፣ በምዕራብ አባያ፣ በድሬ ደዋ፣ በብላቴ፣ በቀበሪዳሀር፣ በአርባምንጭ፣ በመኤሶ፣ በአሶሳና አካባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 35.0-43.5 ዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል (ካርታ4) ፡፡





ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር



ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን

## 1.2 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የማርች ወር በተለይም በመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን ነገር ግን በሁለተኛው አስር ቀናት እና በሶስተኛዉ አስራ አንድ ቀናት ከፍተኛ የእርጥበት መጨመር እንደነበረ የተሰበሰቡ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያሳያሉ። ይህም ሁኔታ የበልግ ሰብል በስፋት አምራች ለሆኑት ለደቡብ ምእራብ፣ ለሰሜን ምስራቅ እና ለመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማከናወንና የተለያዩ የበልግ ወቅት ሰብሎችን ለመዝራት እንዲሁም የረጅም ጊዜ ሰብሎችን አስቀድመው ለሚዘሩ አካባቢዎች የማሳ ዝግጅት ለማካሄድ አዎንታዊ ሚና ነበረው፡፡ በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላትና ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ሚና የነበረው ሲሆን የአፈር ውስጥ እርጥበትን ከማሻሻልና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት አስተዋጽኦ የሚያበረክቱ ምንጮችን ከማጎልበት አንጻር በወሩ ውስጥ የተገኘው እርጥበት ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረዉ (ካርታ 5) ፡፡





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 1.3 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የማርች ወር የነበረው የእርጥበት ሁኔታ በአብዛኛው በኦሞ ጊቤ፣ በስምጥ ሸለቆ፣ በገና ሌዳዋ፣ በዋቤ ሸበሌ፣ በባሮ አኮቦ፣ በላይኛው እና መካከለኛው አዋሽ፣ በላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እርጥበት እስከ ከፍተኛ እርጥት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በአብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ በታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በመካከለኛው ገናሌ ዳዋ፣ እና በላይኛው ዋቢ ሸበሌ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ ይህም ሁኔታ በተፋሰሶች ያለውን የውኃ ሀብት እንዲጨምር ያደረገ ሲሆን በተለይም የመስኖ እና የሀይል ማመንጫ ግድቦች ከመደበኛወ ጋር የተቀራረበ የውኃ መጠን እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር አዎንታዊ ሚና ነበረው። በአንጻሩ ግን የአፋር ደናክል፣ የታችኛው አባይ፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ኦጋዴን እና አይሻ በደረቅ ሁኔታ ስር እንደነበሩ የውኃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ (ካርታ 6) ፡፡




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከማርች 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.1 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በአፕሪል ወር ከዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት መጠናከር ጋር ተያይዞ ከተቀሩት የበልግ ወራት አንጻር በጎላ መልኩ የዝናብ መጠንና ሥርጭቱ በብዙ ሥፍራዎች ላይ የሚስፋፋበት ወር ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ለጎርፍ መፈጠር አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

በመጪው ወር ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ የሚያደርጉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እንደሚጠናከሩና ከዚህም ጋር ተያይዞ ከቀደሙት ሁለት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ ዝናብ በብዙ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊያስከትል የሚችል ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር ይጠበቃል (ካርታ 7) ።




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. ከኤፕሪል 1-30, 2025 የሚኖረዉ የዝናብ መጠን ከረጅም ጊዜ አማካይ ጋር ሲነፃፀር



ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.2 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥለው የኤፕሪል ወር ከቀደሙት ሁለት የበልግ ወራት በመጠንም ሆነ በሥርጭት የተሻለ እርጥበታማ ሁኔታ (Moist condition) በአብዛኛዎቹ የበልግ ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ይኖኖል፡፡ ይህም ሁኔታ የበልግ አብቃይ እና ተጠቃሚ አካባቢዎች ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል። በተለይም ከማርች ወር መግቢያ ጀምሮ በተከታታይ ቀናቶች እርጥበት እያገኙ በነበሩ ስፍራዎች ቀደም ብለው ለተዘሩና በቡቃያና በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ላሉ የበልግ ሰብሎችም ሆነ ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እንዲሁም በደቡብና ደቡብ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች እንደሚኖር የሚጠበቀው እርጥበታማ ሁኔታ እንደ ቦረና እና ጉጂ ለመሳሰሉ የከፊል የአርብቶ አደር አካባቢዎች ዘር ለመዝራትም ሆነ ለእንስሳት የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በተለያየ ምክንያቶች የበልግ ወቅት የእርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለጀመሩና የረጅም ጊዜ ሰብሎችን ለመዝራት የሚጠበቀው እርጥበት አመቺ ሁኔታን እንደሚፈጥር ከግንዛቤ በማስገባት በቂ ግብዓቶችን ለመጠቀም ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ከበልግ ዝናብ የመዋዥቅ ባህርይ የተነሳ በአንዳንድ እርጥበት አጠር አካባቢች ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት ሊከሰት ስለሚችል የሚገኘውን እርጥበት በማከማቸት እና እርጥበትን በማሳ ወስጥ እንዲቆይ የማደረግ ሰራዎችን ለማከናወን ዝግጅት ያስፈልጋል። በሌላ መልኩ በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከባድ ዝናብ እንደሚኖርና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ ሊፈጠር ስለሚችል አርሶ አደሮች ጎርፎች መደበኛ መፋሰሻቸውን ተከትለው እንዲፈሱ የማድረግ ተግባራትንና በተለይም አንዳንድ ውሃ ገብና የአፈር ፀባያቸው በቀላሉ ውሃውን በማያሰርግባቸው አካባቢዎች ባሉ ማሳዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት መብዛትን ሊያስከትልና በማሳዎች ላይ ውሃ እንዲተኛ ሊያደርግ ስለሚችል ተገቢው ትኩረት ተደርጎ የበዛውን ውሃ በቀላሉ ለማጠንፈፍና ለማስወገድ የሚያስችሉ ዘዴዎችን ከወዲሁ ሊተገበሩ ያስፈልጋል፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## 2.3 እ.ኤ.አ ከኤፕሪል 1 እስከ 30/2025 የሚኖረው የአየር ጠባይ በውኃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚጥለው የኤፕሪል ወር በአብዛኛው የበልግ ተጠቃሚ በሆኑት የኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋ፣ ባሮ አኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ እና የአፋር ደናክል ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት መጠን ያገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር የውኃ መጠን እንደሚያሻሽል ይጠበቃል። በተለይም የበልግ ዋነኛ እርጥበት ተጠቃሚ የሆኑ እንደ መልካ ዋከና ያሉ ግድቦች የተሻለ እርጥበት እንዲሚያገኙ ይጠበቃል። በሌላ በኩል የሚኖረው ከፍተኛ እርጥበት ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ እንደ ዋቢ ሸበሌ፣ አዋሽ፣ ኦሞ ጊቤ እንዲሁም ስምጥ ሸለቆ ተፋስሶች ውስጥ የሚገኙ የከተማም ይሁን ረባዳማ የገጠር አካባቢዎች ላይ ቅፅበታዊ ጎርፍ ሊያስከትልና ጉዳት ሊያደርስ ስለሚችል አሰፈላጊ የቅድመ ጥንቃቄ ስራ ማከናወን ያሰፈልጋል። በተጨማሪም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑ ከተሞች የመንገዶች በውኃ መጥለቅለቅ እና የትራፊክ መጨናነቅ ሊያሰከትል ይችላል፡፡ በመሆኑም የጎርፍ ማፋሰሻ ቦዮች በጠጣር ቆሻሻ እንዳይዘጉ ክትትል ማድረግ እና ማጽዳት ያስፈልጋል። በሌላ በኩል  እርጥበት አጠር የሆኑ አካባቢዎች የዝናብ ውሃ ማሰባሰብያ ዘዴዎች በመጠቀም የውኃ ሀብት አቅምን ለማሳደግ ከወዲሁ የውሃ ማሰብሰብ ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል። የተቀሩት ተፋሰሶች ማለትም መረብ ጋሽ፣ የመካከለኛው እና ታችኛው አዋሽ እንዲሁም ተከዜ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር ይቆያሉ፡፡



ስልክ+2511155383394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et